የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 እና 16

1. በምዕራፍ 15 ላይ ያለው የጠፋው ልጅ ታሪክ ላይ የልጆቹ ምሳሌነት ለየቱ ነው?
ሀ) ትልቁ ልጅ የጻሐፍት ፈሪሳውያን፣ ትንሹ ልጅ የኃጥአን መጸብሓን
ለ) ትልቁ ልጅ የባሕታውያን፣ ትንሹ ልጅ የሰብአ ዓለም (በዓለም የሚኖሩ ሰዎች)
ሐ) ትልቁ ልጅ የመላእክት ትንሹ ልጅ የደቂቀ አዳም (የሰው ልጆች)
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

2. ከሚከተሉት ታሪኮች ውስጥ በሉቃስ ወንጌል ላይ ብቻ ተጽፎ የሚገኘው የትኛው ነው?
ሀ) የጠፋው በግ ለ) የጠፋው ልጅ ሐ) ስለንጉሥና አገልጋዮቹ መ) ሀ እና ለ

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚችል አገልጋይ የለም” ሲል ጌቶች ያለው እነማንን ነው?
ሀ) እግዚአብሔር እና የሚያመልኳቸው ጣዖቶች
ለ) ጣዖት እና ገንዘብ
ሐ) እግዚአብሔር እና ገንዘብ
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

4. በምዕራፍ 16 ላይ ያለው ታሪክ ላይ መጋቢው ጌታው ሊያባርረው እንደሆነ ሲያውቅ ምን አደረገ?
ሀ) የጌታውን ባለዕዳዎች ጠርቶ ዕዳቸውን ቀነሰላቸው
ለ) ጌታውን እንዲምረው ሄዶ ለመነው
ሐ) ከጌታው ገንዘብ ላይ ለራሱ የሚሆን ሰርቆ ወሰደ
መ) ሀ እና ለ

5. በምዕራፍ 16 ላይ ያለው ታሪክ ላይ ያለው የሹሙ ምሳሌነት ለየቱ ነው?
ሀ) ንስሐን የማያስተምሩ፣ ነገር ግን በጽኑ በታመሙ ጊዜ የነፍስ ልጃቸውን ጠርተው ቀኖና ሰጥተው “እኔ እኩሉን እጾምልሃለሁ” ብለው ቀኖናውን ያቀለሉለት መምሕረ ንስሐ
ለ) ሥልጣኔን ከመቀማቴ በፊት የምችለውን ያክል ዘርፌ ለራሴ ልውሰድ የሚል ባለሥልጣን
ሐ) ጌታ ነፍሴን ከስጋዬ ሳይለያት በፊት ለነዳያን መጽውቼ ለነፍሴ ልትረፍ ብሎ የሚያስብ አንድ ባለጸጋ
መ) ሀ እና ሐ

6. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ታናሹ ልጅ ወደ አባቱ ቤት በተመለሰ ጊዜ ታላቁ ልጅ በየት ነበር?
ሀ) በጭፈራ ቤት ለ) በእርሻ ሐ) በምኩራብ መ) በመዝናኛ ቦታ

7. ነዌ ስንት ወንድሞች ነበሩት?
ሀ) 10 ለ) 5 ሐ) 2 መ) መልሱ የለም

8. ነዌ አብርሃም አልዓዛርን ወደ ዘመዶቹ እንዲልከው የጠየቀበት ምክንያት ምን ነበር?
ሀ) የሚያስተምራቸው ስላልነበረ
ለ) ከሙታን አንዱ ወደ እነርሱ ሄዶ ካልነገራቸው ንስሐ አይገቡም ብሎ
ሐ) እሱ ወዳለበት የስቃይ ቦታ እንዳይመጡ
መ) ለ እና ሐ

9. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ አብርሃም "... በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል አለ" ሲል ገደል የተባለው ምንድነው?
ሀ) ጭካኔ ለ) የእግዚአብሔር ፍትሕ ሐ) ሰማይ መ) ይህች ዓለም

10. በአልዓዛርና በነዌ ታሪክ ውስጥ የነዌ መጨረሻ ምን ሆነ?
ሀ) በሲዖል ሳለ አብርሃም አዝኖ አልዓዛርን ውሃ እንዲያጠጣው ላከለት
ለ) በሲዖል ሳለ ስለተጸጸተ ነፍሱ ተምራ ወደ ገነት ሄደች
ሐ) ለዘመዶቹ እንዲያስተምር ተላከ
መ) መልሱ የለም

11. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ታናሹ ልጅ ወደ ሩቅ ሀገር ሲሄድ ምን ገጠመው?
ሀ) ገንዘቡን ጨረሰ
ለ) በሃገሩ ጽኑ ረሃብ መጣ
ሐ) ሃብቱ እየበዛለት እጅግ ባለጸጋ ሆነ
መ) ሀ እና ለ

12. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ባለው የጠፋው በግ ምሳሌ ላይ የጠፋውን በግ ሲያገኘው ምን አደረገው?
ሀ)እየመታ እና እየገረፈ ከዘጠና ዘጠኙ ጋር ጨመረው
ለ)ሸጠው
ሐ)አርዶ በላው
መ) በትከሻው ላይ ተሸከመው

13. በሰማያት ፍጹም ደስታ ሚደረገው መቼ ነው?
ሀ)ኀጢአተኛ ንስሐ ሲገባ
ለ)በጎች ሲጠፉ
ሐ) ጻድቃን ኑሮአቸውን ሲኖሩ
መ)ሁሉም

14. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ያለው የድሪም ምሳሌ ላይ ስንት ድሪም እንደጠፋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ?
ሀ)2 ለ)1 ሐ)9 መ)10

15.ድሪም ምንድን ነው?
ሀ)ሳንቲም ለ)የአንገት ሀብል ሐ)የእጅ አምባር መ)ለ እና ሐ

16.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ከሰጣቸው ሶስት ምሳሌዎች ውስጥ አውቆ በፈቃዱ ሊጠፋ የሚችለው የቱ ነው?
ሀ)የጠፋው በግ
ለ)የጠፋው ድሪም
ሐ)የጠፋው ልጅ
መ)ሀ እና ሐ

17.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ታላቁ ልጅ ታናሽ ወንድሙ እንደተመለሰ እና የሰባው ፍሪዳ እንደታረደለት ሲሰማ ምን አደረገ?
ሀ)ወንድሙን ሮጦ አቀፈው
ለ)ከአባቱ ጋር ደስ አለው
ሐ)ወደ እርሻው ተመለሰ
መ)አልገባም ብሎ ከውጭ ተቀመጠ

18.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ ጌታችን በተናገረው ምሳሌ ላይ የአልዓዛር ምኞት ምንድን ነበር?
ሀ)የባለጸጋውን ሀብት ማግኘት
ለ)ከባለጸጋው ፍርፋሪ መጥገብ
ሐ)እንዲሁ መኖር
መ)ሁሉም

19.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ ባለጸጋው በሞተ ጊዜ ከማን ጋር ተነጋገረ?
ሀ)ከእግዚአብሔር ለ)ከሙሴ ሐ)ከአልዓዛር መ)ከአብርሃም

20. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ ባለጸጋው በቅደም ተከተል ለማን ለማን ለመነ?
ሀ)ለራሱ፣ ለወንድሞቹ
ለ)ለሀገሩ፣ ለራሱ፣ ለሚስቱ
ሐ)ለቤተሰቡ፣ ለሀገሩ
መ)ለማንም

21.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 የሙቶው በግ ባለቤት አንዲ በግ ስትጠፋ ዘጠና ዘጠኙን በየት ትቷቸው አንዲን ሊፈልግ ሄደ?
ሀ)በተራራ ለ)በቤቱ ሐ)ከእርያዎች ጋር መ)በምድረ በዳ